# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

***ተዛማጅ ሠነዶች፦*** ACA, IOI-RA, JEE, JGA, JGA-RA, JGA-RB, JGA-RC, FAA
***ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦*** Chief Operating Officer; Chief Academic Officer

## የተማሪዎች ዝውውር እና አስተዳደራዊ ምደባዎች

I. **ዓላማ**

በካውንቲው ውስጥ የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ (የተማሪ ዝውውር) እና አስተዳደራዊ ምደባዎችን በተመለከተ የአሠራር ስርአት ለመዘርጋት።

II. **ዳራ**

ተማሪዎች በመኖሪያ አካባቢያቸው ባለው ትምህርት ቤት ወይም በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ምክንያት በተመደቡበት ትምህርት ቤት መከታተል ይጠበቅባቸዋል። በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ መመሪያ JEE ላይ እንደተገለጸው፣የተማሪ ዝውውር፣ የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ (COSA) አንድ ተማሪ በአካባቢው(ዋ) ከሚገኘው ትምህርት ቤት ውጭ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የመግባት ጥያቄ በወላጅ/አሳዳጊ/ ሊቀርብ ይችላል። ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ (18 (አካለ መጠን የደረሰ(ች) ተማሪ ወይም እድሜው(ዋ)18 ዓመት ከመሙላቱ በፊት ከወላጅ ቁጥጥር የወጣ(ች) ተማሪ) ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የት/ቤት ምደባ ዝውውር ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

III. **ትርጉም**

A. የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ከተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት ሌላ ትምህርት ቤት ከሆነ። በተማሪው(ዋ) ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ምክንያት የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ሆኖ ካውንቲ አቀፍ፣ሪጅናል፣ወይም ሌላ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ፣በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ፣ ወይም አስተዳደራዊ ምደባ ከሆነ። አንድ ተማሪ (COSA) ከተፈቀደለ(ላ)ት በኋላ የተጠየቀው ትምህርት ቤት ምድብ መማሪያ ቦታ ይሆናል።

B. የአካባቢ ትምህርት ቤት ማለት በተማሪዎች መኖሪያ አካባቢ የሚገኝ ትምህርት ቤት ነው።

IV. **የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ እንዲደረግ (COSA) ጥያቄ የሚቀርብበት የጊዜ ሰሌዳ እና የማመልከቻ አቀራርብ ሂደት**

A. የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት

1. ከተማሪ የመኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት ውጪ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ዝውውር ለመጠየቅ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ብቁ ተማሪዎች የተማሪ ዝውውር ሂደት፣የግዜ ገደብ፣ እና የዝውውር መጠየቂያ ቅጽ የያዘ አመታዊ COSA ቡክሌት MCPS ድረ ገጽ ላይ ወይም ከመኖሪያ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት ማግኘት ይችላሉ።

2. MCPS ቅጽ 335-45፣ COSA ጥያቄ፣ በእያንዳንዱ MCPS ትምህርት ቤት እና MCPS ድረ ገጽ ላይ፣ በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል።

B. የጊዜ ገደብ

1. COSA ጥያቄ ለማቅረብ የቦርድ ፖሊሲ JEE፣የተማሪ ዝውውር በማክበር በየዓመቱ በጃኑዋሪ ወር መጨረሻ ላይ COSA ቡክሌት ለትምህርት ቤቶች እና ለማህበረሰቡ የሚሠራጭ ሲሆን በየአመቱ COSA የጥያቄ አቀራረብን ሊያሻሽል ይችላል።

2. የቀረበው COSA ጥያቄ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተማሪዎች በአባቢያቸው ትምህርት ቤት መመዝገብና መከታተል አለባቸው።

3. COSA ቡክሌት ላይ ከተጠቀሰው የመጨረሻ ቀን በፊት የተሞላው MCPS ቅጽ 335-45 ለተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር/ተወካይ መድረስ አለበት።

    a) የተማሪው(ዋ) መኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር/ተወካይ የተማሪው(ዋ) መኖሪያ አካባቢ መሆኑን በማረጋገጥ የቀረበውን ጥያቄ ቅጽ ይፈርማል/ትፈርማለች። እንዲህ ዓይነቱ ፊርማ የቀረበውን ጥያቄ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ማረጋገጫ ማለት አይደለም።

    b) የተሞላውን ቅጽ የተማሪው(ዋ) መኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት ወደ ተማሪ ፐርሶኔል ሠራተኛ እና የተማሪዎች የትምህርት ክትትል አገልግሎት ክፍል (DPPAS) ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች።

    c) ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት DPPAS ግምገማውን ያጠናቅቃል።

4. የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኙ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች (ለምሳሌ�:- የንግግር እና ቋንቋ፣ የቤት ትምህርት ሞዴል፣ በሰዓት የሚመደብ የሰው ኃይል፣ ወይም የትምህርት እና የአካዳሚክ ጉድለት አገልግሎት) የመሳሰሉት መደበኛውን COSA አሠራር መከተል አለባቸው።

    a) የተማሪው(ዋ) ግለሰባዊ ትምህርት ፕሮግራም በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማይሰጡ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት ከሆነ፣ ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ፡ COSA ቅጽ ላይ ተማሪው(ዋ) በልዩ ፕሮግራም የልዩ ትምህርት አገልግሎት እያገኘ(ች) መሆኑ(ኗ)ን ገልፀው ተጨማሪ COSA ጥያቄ የቀረበበትን ምክንያት የሚያረጋግጡ ተገቢ ሰነዶችን ማቅረብ አለባቸው።

    b) በሁሉ ት/ቤቶች የማይገኙ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ከሚያገኙ ተማሪዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች የሚሰጡት ከጁላይ 1 በኋላ ነው።

5. ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ DPPAS ያቀረበውን COSA ጥያቄ በተመለከተ ተቀባይነት ማግኘቱን ወይም ውድቅ መደረጉን የሚገልጽ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

6. የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ማግኘቱን ወይም ውድቅ መደረጉን ለአካባቢ ት/ቤት እና ለተጠየቀው ት/ቤት ይገለጽላቸዋል።

V. ***ወዲያው መፅደቅ ያለበት የተማሪዎች ዝውውር***

የሚከተሉት አይነት የተማሪዎች የዝውውር ጥያቄዎች በቀጥታ ይጸድቃሉ፥ ነገር ግን ለመዝገብ አያያዝ እንዲያመች MCPS ቅጽ 335-45 COSA ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፡-

A. የተቀናጁ ትምህርት ቤቶች በ COSA ዓላማ እንደ አንድ ትምህርት ቤት ይቆጠራሉ። ነገር ግን ተማሪዎች በተፈቀደላቸው COSA በተቀናጀ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ከሆነ፣ ከፍ ባለው አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመማር አዲስ MCPS ቅጽ 335-45 COSA ጥያቄ (ይህ በቀጥታ ይፅድቃል) ማስገባት አለባቸው። እያንዳንዱ ማቀናጀት በዝውውር ተግባር ላይ ተፅእኖ ማድረግ የሚችሉ ልዩ ጠባዮች አሉት።

B. በሞነከሲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መከታተል ለሚፈልጉ በፑልስቪል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተመደቡ ተማሪዎች MCPS ቅጽ 335-45፣ COSA ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው፣ ይህ ወዲያውኑ ተቀባይነት ይኖረዋል።

C. ለዳውን ካውንቲ ኮንሰርቲየም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ልዩ ፕሮግራሞች ከአካባቢው ውጪ ያሉ ተማሪዎች በዕጣ ምርጫ ሂደት ውስጥ በመሳተፍ ዳውንካውንቲ ኮንሰርቲየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መግባት ይችላሉ።

VI. ***ወደ ተማሪ የመኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት መመለስ***

A. ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ በማንኛውም ጊዜ ወደ መኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት ለመመለስ መምረጥ ይችላል/ትችላለች –

1. COSA በተፈቀደበት ትምህርት ቤት እየተከታተለ(ች) ከሆነ፣ ወይም

2. በካውንቲ አቀፍ ወይም ሪጅናል ፕሮግራም ወይም በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ የተለየ ፕሮግራም የሚከታተል/የምትከታተል ከሆነ(ች)።

3. በካውንቲ አቀፍ ወይም በሪጅናል ፕሮግራሞች ውስጥ በመሳተፋቸው ምክንያት በአካባቢያቸው ከሚገኝ ትምህርት ቤት ተለይተው በሌላ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በዚህ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ ካቆሙ ወደ አካባቢ ትምህርት ቤታቸው መመለስ ይጠበቅባቸዋል።

B. ተማሪዎች ወደ መኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት ስለሚመለሱበት ሁኔታ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳዳሪ እንደሚከተለው ይወሰናል፡-

1. በ IEP ምክንያት ከተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ወደ መኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት የመመለስ ጉዳይ በልዩ ትምህርት ጽህፈት ቤት አማካይነት የጉዳዮ ሁኔታ በዝርዝር እየታየ ይወሰናል።

2. ክፍል VII ላይ እንደተገለጸው በአስተዳደራዊ ምደባ ምክንያት ከተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ወደ መኖሪያ አካባቢ ትምህርት ቤት መመለስ።

3. በተገቢ ምክንያት የተማሪው(ዋ) COSA እንዲሰርዝ ርእሰ መምህሩ(ሯ) DPPAS ዳይሬክተርን መጠየቅ ይችላል/ትችላለች። ለደኅንነት የማያሰጋ ከሆነ፣DPPAS ዳይሬክተር ለወላጅ/አሳዳጊ/ለብቁ ተማሪ ርእሰ መምህር/ተወካይ ያሳወቀ(ች)ው ማንኛውንም ስጋት ያለ እንደሆነ፣ ያሉትን ድጋፎች እና ተገቢ የባህርይ ማቅናት ጣልቃገብነት ስልቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ለተማሪው(ዋ) እንዲፈቅድ ለማድረግ መሞከሩን ከግምት ውስጥ በማገባት የጣልቃገብነት ድጋፎቹ ላይ ማቆየት ውጤት የማያስገኝ/ያልተሳካ ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አወንታዊ የመማሪያ አካባቢን ለመጠበቅ አግባብ እንዳልሆነ ይወስኗል።

4. ከተራዘመ እገዳ በኋላ COSA ጥያቄ ተቀባይነት ስለማይኖረው ከሚመለከታቸው የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን ጋር በመመካከር DPAS ዳይሬክተር ስለ ጉዳዩ ይወስናል።

C. አንድ ተማሪ COSA እንደገና ማመልከት ሲኖርበት

1. በአንዳንድ ሁኔታዎች፣COSA ለአንድ ዓመት ብቻ ሊገደብ ይችላል።

a) የትምህርት አመቱ ሳይጠናቀቅ አንድ ቤተሰብ ወደ ሌላ አካባቢ በሚዛወርበት ጊዜ፣ (የቦርድ ፖሊሲ JEE፣ የተማሪ ዝውውር ክፍል C.1.b ላይ ከተቀመጡት ልዩ ሁኔታዎች ጋር) የትምህርት አመቱን ለማጠናቀቅ COSA ሊሰጥ ይችላል።

b) እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ብቁ ተማሪዎች ለሚቀጥለው ዓመት በተመደቡበት ትምህርት ቤት ለመቀጠል COSA ካላገኙ በስተቀር፣ተማሪዎቹ ለሚቀጥለው የትምህርት አመት በመኖሪያ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት መመዝገብ አለባቸው።

2. ከዚህ በላይ ካልተገለጸ በስተቀር፣COSAs ተማሪው(ዋ) በዚያው ትምህርት ቤት እንዲያጠናቅቅ ለመፍቀድ በቂ ዓመታት ይሰጠዋል/ይሰጣታል፣ እና ተማሪዎች በዚያ ሁኔታ ቀጥለው ለመማር COSA እንደገና ማመልከት አለባቸው። የቦርድ ፖሊሲ JEE፣ የተማሪ ዝውውር፣ ክፍል C.3 ይመልከቱ።

VII. **አስተዳደራዊ ምደባዎች**

A. MCPS ለደህንነት ሲባል ተማሪን ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ወይም አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም የመመደብ ስልጣን አለው እና መብቱ የተጠበቀ ነው።

B. OSSWB ሰራተኞች የተማሪዎችን የአካዳሚክ እድገት፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ፣ እና አስተዳደራዊ ምደባዎችን፣ እንዲሁም ማህበራዊ መስተጋብራቸውን የመከታተል ሃላፊነት አለባቸው። በአስተዳደራዊ ምደባ የገቡ ተማሪዎች በተመደቡበት ጊዜ ባለው የአትሌቲክስ እና ሌሎች ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ መብት አላቸው።

C. በትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ (OSSWB) የተጠየቀ አስተዳደራዊ ምደባ

1. ለደህንነት ሲባል በተገቢው OSSWB የአካባቢ ሱፐርኢንተንደንት በኩል የተማሪ አስተዳደራዊ ምደባ እንዲደረግ ርእሰመምህር ሊጠይቅ ይችላል።

2. ከቦርድ ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ማቅናት ጣልቃገብነት፣ደህንነት እና የደህንነት እቅድ ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ OSSWB የአካባቢ ሱፐርኢንተንደንት የተማሪን ዕድሜ፣ በትምህርት ቤት ደህንነት ላይ ተፅእኖ ያደረገውን የቀደመ ስነምግባር፣ ስለ ተማሪው(ዋ) በበቂ ሁኔታ ለመገንዘብ ተጽዕኖ ያደረገ ባህላዊ ወይም የቋንቋ እውነታዎች በማገናዘብ የቀረበውን ጥያቄ የመገምገም ሃላፊነት አለበት።

3. OSSWB የአካባቢ ሱፐርኢንተንደንት ጥያቄውን ለ DPPAS ዳይሬክተር ያቀርባል፣ ዳይሬክተሩ(ሯ) ከርእሰመምህሩ(ሯ) ጋር በመመካከር የተማሪው ሰራተኛ (PPW)፣ የተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት፣ እና ተገቢው OSSWB የአካባቢ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ግምገማ ያደርጋሉ–

a) የተማሪው(ዋ) የትምህርት፣ የህክምና እና የስነምግባር ሪኮርድ፣ እና

b) አወንታዊ የመማሪያ አካባቢን ለመጠበቅ ተገቢ የባህርይ ማረቅ ጣልቃገብነት ስልት ተግባራዊ መደረጉን፣ እንደተሞከረ፣ ወይም እንዳልተሳካ ወይም አግባብ እንዳልነበረ ጥያቄውን መወሰን።

4. DPPAS ዳይሬክተር–

a) OSSWB የተጀመረውን የአስተዳደራዊ ምደባ ጥያቄ ያፀድቃል ወይም ውድቅ ያደርጋል፤ እና

b) ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ፣DPAS ዳይሬክተር ተማሪው(ዋ) መመደብ ያለበ(ባ)ትን ትምህርት ቤት ይመርጣል።

5. የአስተዳደራዊ ምደባን ምክንያት(ቶች) ለመገምገም PPW ከርእሰመምህሩ፣ ከወላጅ/አሳዳጊ እና ከተማሪው ጋር ኮንፈረንስ ሊዘጋጅ ይችላል።

6. ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ በአስተዳደራዊ ምደባ ተማሪን ለማስቀመጥ ከ DPPAS ዳይሬክተር የተሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ይግባኙ በክፍል VIII ላይ የተዘረዘሩትን ሂደቶች ተከትሎ በ15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለዋናው ኦፊሰር ቢሮ መቅረብ አለበት።

7. ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ ተማሪ በክፍል VII.F የተመለከቱትን ሂደቶች በመከተል የትምህርት ቤት ምደባው እንዲገመገም ሊጠይቁ ይችላሉ።

a) ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ የሆነ ተማሪ፥ ተማሪን በአስተዳደራዊ ምደባ የተሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ማለት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ይግባኙ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ የትምህርት ቤት ምደባ ግምገማው ይቆያል።

b) በተጨማሪ ክፍል VIII.D, 3-4 ይመልከቱ።

D. በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ የተደረገ አስተዳደራዊ ምደባ

1. አስተዳደራዊ ምደባ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ሊደረግ ይችላል።

2. ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ ተማሪ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ስለ ተማሪ አስተዳደራዊ ምደባ የሰጡትን ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ይግባኙ በክፍል VIII ላይ የተዘረዘሩትን ሂደቶች ተከትሎ 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቦርድ መቅረብ አለበት።

E. ሪፖርት መደረግ ያለበት ጥፋትን የሚመለከት አስተዳደራዊ ምደባ

ተማሪ ሪፖርት በተደረገ ጥፋት ምክንያት ከመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ከተወገደ(ች)፣እና የተማሪው(ዋ)፣ የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ፣ እና ርእሰ መምህር/የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ፣ እና የውሳኔው ገምጋሚ ቡድን ኮንፈረንስ ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ ርእሰ መምህር ወይም የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ተማሪው(ዋ) ጠበቃ ካለው/ካላት በኮንፈረንሱ ላይ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ የተማሪውን ጠበቃ መጋበዝ እንዳለባቸው የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል።

1. በሜሪላንድ ህግ (የሜሪላንድ ህግ የተብራራ ኮድ የትምህርት አንቀፅ 7-303(a)(6)) መሠረት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ያልተፈፀሙ ጥፋቶች፥ ነገር ግን በትምህርት ቤት ስፖንሰር በተደረጉ ዝግጅቶች ላይ የተፈፀመ ጥፋትን በሚመለከት አንዳንድ የጥቃት ወንጀሎችን ያካተተ ትርጉም ይኖረዋል። እነዚህ የአመጽ ወንጀሎች በዚህ ብቻ ባይወሰኑም ነገር ግን የሚያካትቱት፥ ቤት ወይም ህንፃ ማቃጠል፣ማጥቃት፣ ቤት ሰብሮ መዝረፍ፣ በወንጀለኛ የድርጅት እንቅስቃሴ መሳተፍ፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አደገኛ ንጥረ ነገሮች እና ቁጥጥር የማይደረግባቸው እፅ ንጥረ ነገሮችን መያዝ፣ መሸጥ፣ ማሠራጨት ጋር የተያያዙ ጥፋቶች፣ ከአጥፊ መሳሪያዎች እና የጦር መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፣ እና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን በመጠቀም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን አደገኛ እጾችና ንጥረ ነገሮችን ማምረት፣ማሠራጨት ወይም ማከፋፈል።

2. በሜሪላንድ ደንብ ኮድ (COMAR) 13A.08.01.17.B ላይ እንደተገለጸው ተጨማሪ ሂደቶችም ይከተላሉ፦

    a) ከህግ አስከባሪ ኤጀንሲ አንድ ተማሪ በ ተጠርጥሮ(ራ) በቁጥጥር ስር መዋሉ(ሏ)ን ሪፖርት ከህግ አስከባሪ ኤጀንሲ መረጃ ሲደርሰው/ሲደርሳት፣ የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ በፍጥነት ተማሪው(ዋ) ለሚማርበት/ለምትማርበት ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ተማሪው(ዋ) በእስር ላይ መሆኑ(ኗ)ን እና የተከሰሰ(ች)በትን ጉዳይና ሁኔታ ጭምር መረጃ ይሰጣል። የታሰረ(ች)ው ተማሪ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አማካይነት ህዝባዊ ባልሆነ ትምህርት ቤት የሚማር/የምትማር አካል ጉዳተኛ ተማሪ ከሆነ(ች)፣የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ የክሱን ሁኔታ ጨምሮ ተማሪው(ዋ) በእስር ላይ መሆኑ(ኗ)ን ለት/ቤቱ ርእሰመምህር መረጃ መስጠት አለበት።

    b) የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር፣ አግባብ ካላቸው ሰራተኞች ጋር፣ ለተማሪው(ዋ) ተገቢውን ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚመለከት እና ለሁሉም ተማሪዎች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስተማማኝ የትምህርት ቤት አካባቢን የሚያረጋግጥ እቅድ ማዘጋጀት አለበት። የትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ–

        (1) በእቅድ ዝግጅቱ ላይ እንዲሳተፉ፣ እና

        (2) ዕቅዱን ለማዘጋጀት ጠቃሚ መረጃ እንዲጡ ይጠይቃል።

    c) ዕቅዱ በተማሪው(ዋ) የትምህርት ፕሮግራም ላይ ለውጥ ካመጣ፣ የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ስለ እቅዱ ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ወዲያውኑ ስብሰባ/ኮንፈረንስ ማዘጋጀትና መጥራት አለበት። የእስር መረጃ ከደረሰ በኋላ እቅዱ ከአምስት የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ መደረግ አለበት።

    d) የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር እና የሚመለከታቸው ሰራተኞች እቅዱን እና የተማሪው(ዋ)ን ሁኔታ በመገምገም እንደአግባቡ ማስተካከያ ማድረግ አለባቸው፦

        (1) ጥፋት መፈፀሙን የሚገልፅ ማሳወቂያ ከስቴቱ አቃቤ ህግ እንደደረሰ በፍጥነት፤ ወይም

(2) ከስቴቱ ኢቃቤህግ ማሳወቂያ በመጠባበቅ ላይ ያለ ቢሆንም፣ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ

e) ወላጅ/አሳዳጊ በእቅዱ ላይ ስለተደረጉ ማናቸውም ማስተካከያዎች ይገለጽላቸዋል።

F. አስተዳደራዊ የትምህርት ቤት ምደባ

1. DPPAS ዳይሬክተር ተማሪው(ዋ)ን አስተዳደራዊ ምደባ ወደተደረገበት ት/ቤት ይመድባል። የትምህርት ቤት ምደባ ሲደረግ የትምህርት ቤት አቅምን፣ መጓጓዣን እና ለተማሪው(ዋ) አጠቃላይ የትምህርት ስኬት እድሎች፣ አወንታዊ የአቻዎቻቸው ግንኙነቶችን እና በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ጭምር ግምት ውስጥ ያስገባል።

2. PPW ከወላጅ/አሳዳጊ እና ከተማሪው ጋር የሚያደርገው ስብሰባ/ኮንፈረንስ ተማሪው(ዋ) ሊመደብባቸው የሚችሉ ትምህርት ቤቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይችላል።

3. ከት/ቤት የተራዘመ መታገድን ተከትሎ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ አስተዳደራዊ ምደባ አስፈላጊ መሆኑን ሲወስን፣
የ DPAS ዳይሬክተር የሚከተሉትን ያደርጋል፦

a) የተራዘመው እገዳ ሲጠናቀቅ ተማሪው(ዋ) በአዲስ ትምህርት ቤት አስተዳደራዊ ምደባ እንደሚደረግለ(ላ)ት ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች/ብቁ ለሆነ(ች) ተማሪ በጽሁፍ ማሳወቅ፣ እና

b) የእገዳው ጊዜ ከማለቁ ከአምስት የስራ ቀናት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች አዲሱን የትምህርት ቤት ድልድል በጽሁፍ ማሳወቅ።

4. የትምህርት ቤቱን ምደባ እንዲገመገም ይጠይቁ

ስለ አዲሱ የትምህርት ቤት ምደባ ከተነገረ በኋላ፣ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ ምደባው ለቤተሰብ አላስፈላጊ ችግር ይፈጥራል ብለው ካመኑ ወይም የአቻዎቻቸው ግንኙነቶችን ጨምሮ፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ተሳትፎ ለተማሪው(ዋ) አጠቃላይ የትምህርት ቤት ስኬት እድሎችን የሚከለክል ከሆነ፣ የትምህርት ቤት ምደባው እንዲከለስ መጠየቅ ይችላሉ።

a) ጥያቄው ለሚመለከተው DPPAS ዳይሬክተር በጽሁፍ መቅረብ አለበት።

b) DPPAS ዳይሬክተሩ ጥያቄውን ከገመገመ እና አዲሱ የትምህርት ቤት ምደባ ለቤተሰብ አላስፈላጊ ችግር እንደማይፈጥር ከታመነ ወይም ለተማሪው(ዋ) አጠቃላይ የትምህርት ቤት ስኬት እድሎችን የሚከለክል ከሆነ፣ ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ በዚህ ደንብ ክፍል VIII C. መሠረት (COSA) ይግባኝ የማቅረብ ሂደት መከተል አለበት።

VIII. ይግባኝ

| COSA ውድቅ ማድረግ | COSA መሠረዝ | OSSWB አስተዳደራዊ ምደባ | በሱፐር ኢንተንደንት የተደረገ አስተዳደራዊ ምደባ | ምደባ የተደረገበት ትምህርት ቤት (አስተዳደራዊ ምደባዎች) |
|---|---|---|---|---|
| ውድቅ የተደረገበት ውሳኔ በ15 ቀናት ውስጥ ለሱፐር ኢንተንደንት | ውሳኔው በተሻረ 15 ቀናት ውስጥ ለሱፐርኢንተንደንት | የምደባ ውሳኔው በተደረገ 15 ቀናት ውስጥ ለሱፐርኢንተንደንት | ከዚህ በታች ይመልከቱ (በቀጥታ ለቦርዱ ይግባኝ ስለማቅረብ) | ምደባ የተደረገበትን ትምህርት ቤት DPPAS ዳይሬክተር አማካይነት እንዲገመገም መጠየቅ። በ DPAS ውሳኔ ካልረኩ፣ DPAS ውሳኔ በሰጠበት 15 ቀናት ውስጥ ለሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ያቀርባሉ። |
| ከሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ውሳኔ ከተሰጠ 30 ቀናት ውስጥ ለቦርድ ይግባኝ ማቅረብ | የሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ውሳኔ በ 30 ቀናት ውስጥ ለቦርድ ይቀርባል | የሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ውሳኔ በተሰጠ 10 ቀናት ውስጥ ለቦርድ | ከሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ውሳኔ በተሰጠ 10 ቀናት ውስጥ ለቦርድ | የሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ውሳኔ በተሰጠ 30 ቀናት ውስጥ ለቦርድ |

A. ይግባኝ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

1. የዲስትሪክት ኦፕሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ ለ COSA ውሳኔ እና አስተዳደራዊ ምደባ ይግባኝ (በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከተደረጉት አስተዳደራዊ ምደባዎች በስተቀር)።

2. COSA ውድቅ ካደረገ በኋላ፣ COSA የሻረው ወይም አስተዳደራዊ ምደባ ይግባኝ በጽሁፍ መቅረብ አለበት እና የውሳኔው ደብዳቤ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ (በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የተደረገው አስተዳደራዊ ምደባ፣ክፍል VIII.E.1 ይመልከቱ)።

3. ይግባኙ ውሳኔው እንዲቀለበስ የሚያስፈልግበትን ምክንያት(ቶች) መግለጽ እና ሊታሰብባቸው የሚያስፈልጓቸውን ተጨማሪ መረጃዎች ማካተት አለበት።

4. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ያሉትን ሁሉንም መረጃዎች ይመረምራል።

5. ምንም እንኳን ጉዳዮች የሚገናዘቡት በቀረቡት ሠነዶች እና በስልክ በሚካሄዱ ኮንፈረንሶች ላይ ተመስርቶ ቢሆንም፣ በዋና የሥራ ኃላፊ ይግባኝ ሰሚ አማካይነት በአካል ተሰብስቦ ኃሳብን የመግለጽ እድል ማዘጋጀት ይቻላል።

6. በአንድ ጊዜ የሚስተናገዱትን የይግባኞች ብዛት፣ውስብስብነት እና የጊዜ ርዝመት ግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔዎች ወዲያውኑ ይደረጋሉ።

B. የ COSA ጥያቄ ውድቅ የተደረገበትን ይግባኝ መጠየቅ

1. ውድቅ የተደረገን የ COSA ጥያቄ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ይግባኝ ማለት ይችላል።

2. ውድቅ የተደረገ የ COSA ውሳኔ ይግባኝ በሂደት ላይ እያለ ከአስተዳደራዊ ምደባዎች በስተቀር ተማሪው(ዋ) በአካባቢው9ዋ) ትምህርት ቤት መግባት እና ትምህርት መከታተል አለበ(ባ)ት።

3. ከጁላይ 1 በፊት ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ የቀረቡት ውድቅ የተደረጉ COSA ውሳኔዎች ት/ቤት ከመጀመሩ በፊት ይወሰናሉ።

C. የተሻረ COSA ውሳኔ ይግባኝ

1. የተማሪ COSA ከተሰረዘ፣ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ይግባኝ ማለት ይችላል።

2. ይግባኙ በሚካሄድበት ወቅት ተማሪው(ዋ) በተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት (ማለትም፥ ተማሪው(ዋ) COSA የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት) ተመዝግቦ ሊቆይ ይችላል።

3. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ስረዛው ተገቢ መሆኑን ከደገፉ፣ተማሪው(ዋ) ወደ አካባቢ ትምህርት ቤት ይመለሳል-ትመለሳለች። ወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ ለትምህርት ቦርድ ይግባኝ ለማለት ከፈለጉ ተማሪው(ዋ) በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ይቆያል/ትቆያለች።

D. የአስተዳደራዊ ምደባ ይግባኝ

1. አስተዳደራዊ ምደባው በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተነሳሽነት የተከናወነ ካልሆነ በስተቀር (ክፍል VIII.E.1 ይመልከቱ) በአስተዳደራዊ ምደባ ተማሪን የመደልደል ውሳኔ ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ በይግባኝ ሊቀርብ ይችላል።

2. ተማሪው(ዋ) በአስተዳደራዊ ምደባ የተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት በመጀመሪያ DPPAS ዳይሬክተሩ እንዲገመገም ከተጠየቀ በኋላ (ክፍል VII.F ይመልከቱ) ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ይግባኝ ማለት ይችላል።

3. VIII.C.3 ላይ ከተገለፀው ሁኔታ በስተቀር በይግባኙ ወቅት ተማሪው(ዋ) በአስተዳደራዊ ውሳኔ በተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት መቆየት አለበ(ባ)ት።

4. አስተዳደራዊ ምደባው የተራዘመ እገዳን ከተከተለ፣ በተራዘመው እገዳ ወቅት ተማሪው(ዋ) በሚማርበት/በምትማርበት ትምህርት ቤት መቆየት ይችላል/ትችላለች፣ ወይም እገዳውን ተከትሎ በተመደቡበት ትምህርት ቤት ሊማሩ ይችላሉ።

E. ለትምህርት ቦርድ ይግባኝ ማቅረብ

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ በጽሑፍ ለትምህርት ቦርድ ይግባኝ ሲቀርብ ትምህርት ቦርዱ ይግባኙን መቀበል አለበት፣

   a) COSA ጥያቄ ውድቅ መደረጉን ወይም COSA መሻርን በተመለከተ ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በተሰጠው የውሳኔ ደብዳቤ ላይ ከተፃፈው 30 ቀናት ውስጥ።

   b) የተማሪን አስተዳደራዊ ምደባ በሚመለከት የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በሰጠው የውሳኔ ደብዳቤ ላይ በተገለፀው 10 ቀናት ውስጥ።

2. አቤቱታ አቅራቢዎች የሚያቀርቡትን ይግባኝ በተቻለ ፍጥነት እንዲያደርጉት ይበረታታሉ።

3. በቦርድ ፖሊሲ BLB ላይ እንደተገለጸው በይግባኝ እና ችሎት የሥርዓት ሕጎች፣የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ቦርዱ ይግባኙን ከማየቱ በፊት ቅጂውን ለይግባኝ አቅራቢው ይላካል።

4. በቦርዱ ይግባኝ ሂደት፣ ተማሪው በትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ/ተወካይ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት በትምህርት ቤቱ መመዝገብ አለበት።

5. በቦርድ ፖሊሲ BLB መሠረት የቦርዱ ውሳኔ፣ ይግባኝ እና ይግባኝ ሰሚ ችሎትን የሚመለከቱ የአሰራር ደንቦች ላይ በተቀመጡት ሂደቶች ላይ በመመስረት በፅሁፍ የሚቀርብ ይሆናል።

የደንቡ ታሪክ፡- የቀድሞው ደንብ 265-2፣ ፌብሩዋሪ 22,1980፣ ጃኑዋሪ 23,1992 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 25,1994 ተሻሽሏል፤ ዲሴምበር 23,1994 ተሻሽሏል፣ጃኑዋሪ 30,1997 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 20,1998 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 2, 1999 ተሻሽሏል፣ የቢሮ ስያሜዎች ጁን 1, 2000፣ ዲሰምበር 6, 2000 ተሻሽሏል፣ ጃኑዋሪ 7, 2002 ተሻሽሏል፣ጃኑዋሪ 10, 2003 ተሻሽሏል፣ ኖቬምበር 29 2006 መጠነኛ ክለሳ ተደርጓል፣ ኖቨምበር 27, 2007 መጠነኛ ክለሳ ተደርጓል፣ ኖቨምበር 17, 2008፣ ጃኑዋሪ 04, 2010 ተሻሽሏል፣ ኖቨምበር 18, 2010 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 12, 2011 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 20, 2012 ተሻሽሏል፣ ኖቨምበር 6, 2013 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 13, 2013 ተሻሽሏል፣ ኤፕሪል 5, 2018 ተሻሽሏል፣ ጃኑዋሪ 7, 2019 ተሻሽሏል፣ ሴፕተምበር 28, 2023 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጅንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning, and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ፌብሩዋሪ 2024